በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ 165/2009 አንቀጽ 22 መሠረት
በመጋዘን የሚገኝ ዕቃ ዋጋ አተማመን

በግብር ዓመት ውስጥ ላልተሸጡ በመጋዘን የሚገኙ የንግድ ዕቃዎች የተደረገ ወጪ የሚሰላው በአማካኝ የወጪ ስሌት ዘዴ(Weighted Average Method) ማለትም በመጋዘን የሚገኘው የእያንዳንዱ ዕቃ ዋጋ በአማካኝ ወጪ እንዲሰላ በሚያስችለው አጠቃላይ ተቀባይነት ባገኘው የሂሳብ አያያዝ ስሌት መሠረት ነው።

የሂሳብ አያያዝ ዑደት እና ሂደቶች

2.1 የሂሳብ አያያዝ ሂደት(Accounting process)

- ❖ የሂሳብ አያያዝ ሂደት በአጭሩ ሲገለጽ

የተፈፀሙ ልውውጦችን በመለየት መነሻ ሰነዶችን በማዘጋጀት በመዝገብ የመመዝገብና ወደ ሌጀር የማወራረስ እንዲሁም በመጨረሻ የተጠቃለሉ የሂሳብ መግለጫዎችን ማለትም የትርፍና ኪሳራ ሂሳብ እና የሀብትና ዕዳ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ተግባራትን የሚያጠቃልል ነው።

በክልላችን የግብር እና ታክስ ህጐች ውስጥ
ለግብር ከፋዮች የተፈቀዱ ደረሰኞች፡-

- የሽያጭ ደረሰኝ (እንደ ግብር ከፋዩ ደረጃ እና የግብይት ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ TOT ወይም VAT የሚያካትት ሊሆን ይችላል)
- የገንዘብ ወጪ ደረሰኝ፣
- ንብረት ገቢ ደረሰኝ፣
- የንብረት ወጪ ደረሰኝ እንዲሁም
- ደረሰኝ ለማይገኝላቸው አቅርቦቶች (አቅራቢዎች) የሚሰጥ ደረሰኝ የሚያካትቱ ሲሆን ከግብር ባለስልጣኑ በሚሰጠው ፈቃድ አሳትሞ በህጉ በተቀመጠው መሠረት በአግባቡ መጠቀም ይኖርበታል።

ሂሳቦችን መመዝገብ (Journalizing)

- ❖ የሂሳብ ልውውጦች ግብይቱ በተካሄደበት ደረሰኝ ላይ የተሰጣቸውን መደብ (ኮድ) እና ዋጋ እንዲሁም ሌሎች መረጃዎችን በማካተት በሂሳብ መዝገብ ላይ መመዝገብ የሚኖርባቸው ሲሆን ይህም በሂሳብ መዝገብ አያያዝ ቅደም ተከተል (ዑደት) ሁለተኛው ወሳኝ ምዕራፍ ነው።
- ❖ ግብር ከፋዩ የሁሉንም የሂሳብ መደቦች ልውውጦች በየጊዜው የሚያዝበትና የመረጃ ምንጮችን (ደረሰኞችን) መሠረት በማድረግ የሚመዘገብበት አንድ ዋና መዝገብ (General/combination Journal) ወይም እንደ ንግድ ባህሪይው የተለያዩ የሂሳብ መዝገቦች (Special journals) መያዝ ይችላል።

<u>ለምሳሌ የዕቃና የአገልግሎት ሽያጭ ገቢ መዝገብ</u>

ተ.ቁ	ገቢው የተሰበሰበበት ቀን'ወር ዓ/ም	ገቢው የተሰበበት ደረሰኝ ቁጥር/Z number		የገቢው ዓይነት						ምርመራ
		ከ	እስከ	ከቢራ ሽያጭ	ከለስላሳ ሽያጭ	ከምግብሽያጭ	ከአልጋ ኪራይ	ጠቅላላ ሽያጭ	ከሽያጩ የተሰበሰበ የተ.እ.ታ 15%	
1	01/11/2013 -									
2	02/12/2013									
3	03/01/2014									
4	04/01/2014									
5	05/01/2014									
6	30/01/2014									
ጠ/ድምር										

Telegram address :- የጌታ ወረዳ ገ/ባለ/ቅ/ጽ/ቤት

:- የገቢ ጥናት/ታ/ት/ኢ/ቅ/ኢ/ዳ